# ጥሪ

ደራሲ፡- ተሾመ ፍሰሐ

ግንቦት **7/1996** ዓ.ም

መነሻ ሀሳቡ፡- ኢትዮጵያዊው በማንነቱ ፍለጋ

መ/ገ/ጽ/ቅ/ጊ/ስ/ት/ቤት
ኪነ ጥበብ ክፍል

ትእይንቱ ሲጀምር መድረኩ ላይ ሰው አይኖም ከመድረኩ ጀርባ የሰው ጭቅጭቅ ይሰማል። የሚነጋገሩት ገበየሁ፣ በለጠ፣ እና እስክንድር ናቸው። እንደሚከተለው ይነጋገራሉ።

ገበየሁ፦ እንዴት አንተ ሰው አይሰማህም? የለም ነው እኮ የምለው! /ባላገር ሰው አነጋገር ለዛ/

በለጠ፦ ስማ በጣም ስለምፈልገው ገብቼ ማየት እፈልጋለሁኝ

ገበየሁ፦ አታምነኝም ማለት ነው?

በለጠ፦ አላምንህም!

ገበየሁ፦ ከሆነ ደግ! ግባና እየው መቼም ሰው ላይ መጣበቅ ልማድህ ነው፣ /ከዚያም በሩ ተከፍቶ /በመናደድ ይናገራል;ወደ ውስጥ ይገባሉ። ገበየሁ ወደ ውስጥ እንደገባ/ ይኸው እየው እሺ የት አለ? ሰለገባህ ምን አመጣህ?

በለጠ፦ /ቤቱን በዐይኑ በደንብ ካማተረ በኋላ/ በቃ ያለ መስሎኝ ነበር ከሌለ የለም ነው

ገበየሁ፦ ምን እንደሁ...... ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል አሉ? ድሮስ ደላላ አይደለህ? ደላላ ሲባል መቼም ችግር አለበት።

በለጠ፦ የምን ችግር?

ገበየሁ፦ የሌለውን አለ የማይገኘውን ይገኛል! ሰለምትሉ ሁሉም እንደናንተው ይመስላችኋል

በለየ፦ ልክ ነዋ በዚህ ምድር የሌለ ነገር ምን አለ ብለህ ነው ?

ገበየሁ፦ ሞልቷል ለምሳሌ የናንተ ውሸታችሁ የሌለ ነው። እስኪ እንደው የለም ስልህ ብታምነኝ ምን ነበረበት ደሞ እዚህ ገብቶ ከመቆም በስተቀር ምን አመጣህ?

በለጠ፦ ምን አስሬ ትደጋግመዋለህ? የዋሸሽኝ ስለመሰለኝ ገብቼ አየሁኝ ሌላ አዲስ ነገር አለው? ደግሞ መቆሜ ካሳሰበህ ልቀመጥ እችላለሁ። /ብሎ ሊቀመጥ ሲል/

ገበየሁ፦ ይሔ ነው ችግር! /እየጮኸ/ ጭራሽ አንተ እሱ ላይ ልትቀመጥ ተነስ! ተነስ!!

በለጠ፦ /በመደንገጥ ከመቀመጫው እየተነሣ/ምነው ምን አለበት?

ገበየሁ፦ ችግር አለበት የትም እንዳህያ ስንትከባለል ውለህ በጌቶች ወንበር ላይ ልትቀመጥ€ ይሔ ድፍረት ሖ!... በል ከፈለክ በርጩማ ላጥ ተቀመጥ! /በጣቱ ወደ በርጩማው እያሳየ/

በለጠ፦ /በመናደድ/ ዋዕ አንተ ዘበኛ ነገርኩህ እሺ በጨራሽ ውዬለ አድርበት በነበረበት ቤት ልታገዝት ትችላለህ?

ገበየሁ፦ ኡ!.. በነበር ቀረ ባክህ ዛሬ አንተ ደላላ ነህ እኔ ደግሞ የዚህ ቤት ጠባቂ ነኝ ኦኬ! /ጭንቅላቱን እየነቀነቀ/

እስክንድር ይገባል

በመ/ገ/ጽ/ቅ/ጊ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤት

ኪነ ጥበብ ክፍል

በለጠ፦ ይሔ ነው ስልጣኔ ጭራሽ እንግሊዘኛ?

ገበየሁ፦ የስ! እግሊዘኛ /አሁንም ጭንቅላቱን እየነቀነቀ / አሁንም እደግምልሃለሁ ከፈለክ ሲዳው! ከልፈለክ ጌራውት! ኦኬ! /ዞር ይልና ደግሞ ለእስክንድር/ እስክንድር ወንበሩ ላይ ቁጭ በል /ይለዋል በአክብሮት/

እስክንድር፦ /እየተቀመጠ/ አመስግናለሁ /ይላል በፈገግታ ተሞልቶ/

በለጠ፡- አሁን መቀባጠሩን ትተህ ወንደሰን ይት እንደሔደ ንገረኝ?

ገበየሁ፡- እኔ ምን አውቃለሁኝ ? ሲመጣ ጠይቀኸዋ?

በለጠ፡- አረ…መልስ! .....ቆይ ግን አንተ የፈረንጅ ሥጋ ነው ወይስ የማድቤት ሽሮ ነው እንዲህ በጥጋብ የወጠረህ?/ እያፈጠጠበት ይጠይቀዋል/

ገበየሁ፡- እሱ አንተን አይመለከትህም ጌቶችን ይጭንቃቸው። ይልእ አስታሰውከኝ የሚሸጥ የበግ ቆዳ ስላለን ደላላ እንፈልጋለን።

በለጠ፡- /በንዴት ከተቀመጠበት ተሰንፈጥሮ ይነሳል በመማታት/ እኔ ነኝ አንተ የቆዳ ደላላ እንዴት ተናናቅን አንተ ዘበኛ /እያለ ሊያንቀው ሲነሣ እስክንድር ጣልቃ ይገባል/

እስክንድር፡- ተው እንጂ ረጋ በል! /ሲለው ዘነኛ በተደፈርኩ ባይነት ስሜት/

ገበየሁ፡- ችግር አለ! ኦ.. ጭራሽ ልትማታ? እኔ ነኝ ገበየሁ አልተዋዋአንማ/ ዱላውን ለድብድብ እያዘጋጀ/ ሰማህ እኔ በአገሬ እንኳን እንዳንተ አይነቱን ኮማሣ ይእርና ወጠምሻውን ጥያለሁ። በዚህ ዱላ አናትህን ተርትሬ እጄን እሰጣለሁ። /ይላል ነገሩን እያጋነነ/ በልና ና ሞክረኛ ና! /ዱላውን እያስተካከለ/

አስክንድር፡- ገበየሁ ለምን ዝም አትልም? ፀብ ምን ያደርግልሃል? /ይለዋል በለጠን ካረጋጋ በኋላ/

ገበየሁ፡- ችግር አለ!... እንዴ አታየውም እራሱ አይደል በጠብ የሚፈልገኝ?

እስክንድር፡- በቃ እሱን ተወውና ወንደሰን እስኪመጣ ትንሽ እንጠብቀው አንተ እዛው ሁን

ገበየሁ፡- ጥሩ ምን አገባኝ! ግን ላንተ ብዬ ነውይ የተውሁት/ ብሎ እየተንጎማለለ ይወጣል ገበየሁ ከወጣ በኋላ እስክንደር ንግግሩን ይጀምራል/

እስክንድር፡- ምን ነካህ? በለጠ ከዚህ የዋህ ባላገር ፀብ ምን አመጣው?

በለጠ፡- እያየህ ትናገረኛለህ? እንደ አባቱ ገዳይ ጠምዶ ይዞኝ ምን ላርገው? ብቻ ተወው ይሄን ጥጋቡን ባላበርድለት እኔ በለየ አይደለሁም። ከወንደሰን ጋር የሚያገናኘኝን ጉዳይ ልጨርስ ብቻ የእንጀራ ገመዱን ነው የምበጥሰው! /በንዴት እየተርገፈገፈ/

እስክንድር፡- ይልቅ እሱን ተውና አሁን ምን ልታደርግ ነው!



በለጠ፡- ምን አደርጋለሁ /ይምጣና ገንዘብ ተቀብዬ እንሔዳለና/ ከንዴቱ በረድ እያለ/

እስክንድር፡- ማለቴ ቢቆይስ? ደግሞም ዛሬ ብር ላይዝ ይችላል እኮ።

በለጠ፡- በሃብታሞች ኪስ ብር ይጠፋል ልትን ነው? ሰሞኑን የዓመት በዓል ስራ ሳይሰቅል አይቀርም /ፈገግ ይላል/ ይልቅ ወንደሰንን ብር ለማስወጣት ስለ አሜሪካን ሕልሙ ማንሣት ብቻ ነው ወይም አብራው ስለምትሔደው ሰለ ዮርዳኖስ ማጫወት ብቻ።

እስክንድር፡- /ፈገግ እያለ/ ወይ በለጠ አንተ መቼም ዘዴ አታጣም በቃ?

በለጠ፡- ምን ላርግ በለህ ነው? ሥራ ቢጠፋ ይሔን ፈጥሮ ሥጋዬን ማሰንበት ያቃተኝ?

እስክንድር፡- እውነት ግን ወንደሰን ያሰበው እንደነበረው አሜሪካን ሊሔድ ነው በቃ?

በለጠ፡- እድሜ ለዲቪ ይበል ይሔው እሱም አንደኛው ሕልሙ ሕልም ከመሆን ባለዘለለ

እስክንድር፡- እንዴት ማለት?

በለጠ፡- ምን እንዴት አለው ብለህ ነው? አባቱ ከዚህ ሀገር እንዲወጣ መች ፈልገው ነበር?

እስክንድር፡- እና ካልፈለጉ እንዴት ፈቀዱለት?

በለጠ፡- እርሳቸው መች ሰጡትና! ይገርምሀል /ነገሩን በማዳነቅ አይነት/ ገና ዲቪ ሲደርሰው እኔን ነበር ያማከረኝ እናም አብራው የምትወጣ ሴት እንዳገናኘው ጠየቀኝ እኔም ከዮርዳኖስ ጋር አገናኘሁት። ታዲያ እሷዋም አሜሪካን ሀገር የመውጣት ጉጉትዋ ቀላል አይምሰልህ የሀብታም ልጅ ብትሆንም በዲቪ ሰበብ ከዚህ ሀገር መውጣት እጅግ ትፈልጋለች። ከዚያም እንዳልኩህ ሁለቱንም አገናኘኋቸው እንግዲህ እሱም ከሰዋ የሚደርሰውን እክል ተነጋግረው ይኸው ፕሮሰሱን ሁሉ ጨርሰው ለመሔድ እየተጠባበቁ ነው እልሃለሁ።

አስክንደር፡- እንዴት ይገርማል? ወንደሰን ግን የተሳሳተ አይመስልህም?

በለጠ፡- እንዴት /በመገረም ይጠይቀዋል/ ቆይ እንዴት መሳሳት?

እስክንድር፡- እስኪ አስበው እዚህ ሀገር ደህና ሕይወት መኖር ይችላል። የአባቱን ንብረት ማስተዳደር ቢችል ብዙ የሥራ ልምድ ያገኝ ነበር። እዚህ አገር አንዳች ሳይሰሩ ኖረው ውጪ ሀገር ሥራ ፍለጋ መሰደዱ እንጃ አግባብ አይመስለኝም።

በለጠ፡- ወይ ልምድ እሱ መች እንዲህ ያልምነ? ቀንና ለሊት የሚያስበው ስለ አሜሪካ ብቻ ነው። የአበቱ ሀሳብማ ትምህርት አንዲማርና እርሳቸውን እንዲያግዝ ብቻ ነበር። ይሔ መከረኛ ዲቪ ቀደማቸው እንጂ።

እስክንድር፡- ግን እኮ የሚመክረው ሰው ያስፈልጋል። ማለቴ ስለ ውጪ ሀገር ሕይወት በደንብ ማወቅና ሊገጥመው ስለሚችል መሰናክል ጠንቅቆ መረዳት ይጠበቅበታል። እንደምታውቀው እዚህ የተለመደ ነገር ሁሉ እሱው ሀገርም ይገጥመኛል ማለት የዋህነት ነው!

በመ/ገ/ጽ/ቅ/ጊ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤት
ኪነ ጥበብ ክፍል

በለጠ፡- ወይ እስክንደር የማያሳስበው ያሳስብሀል ልበል? እሱ እኮ ስለ አሜሪካ አገር ከኛ የበለጠ ያውቃል። አንዴ ይገርምሀል እንደውም እሱ ጋር አይጠፋም በመሆኑም ስለ አሜሪካን ከኔ በላይ ለአሣር ባይ ሆኖዋል። ስለዚህ አትጨነቅ ይልቅ እኔም ደርሶኝ ከዚህ በተገላገልኩ ማለቱ ሳይሻል አይቀርም።

እስክንደር፡- እንዴት?

በለጠ፡- በቃ እኔም ሥራ ሠርቼ መለወጥና የምፈልገውን ማሟላት።

እስክንደር፡- ችግሩ ስራ መናቅ ሆነ እንጂ እዚህስ ሀገር አነስተኛ ሥራዎች መች ጠፍተው ነበር ብለህ ነው?

በለጠ፡- ደግሞ እዚህ ሀገር ሥራ አለ?

እስክንድር፡- አይጠፋም ሥራ እስከተባለ ጭቃ ማቡካትም ሥራ ነበር ለምሳሌ እኔ የምሰራው ሥራ በከንቱ ትንቁታላችሁ

በለጠ፡- ተው ተው እንደተ እንጨት መፈቅፈቅ ሥራ ነው ልትለኝ ነው? ትንሽም ሼም አይዝህም? አቧራ ከመሆንሰእ የዚህ ዘበኛ መቀለጃ መሆን ይመረጣል? በእጁ ዘበኛው በወጣበት አቅጣጫ እያመለከተ/

እስክንድር፡- /በሁኔታው ፈገግ እያለ/ ለኔ ከሥራም በላይ ነው/ እንጀራ አላጣሁበትም ሕይወቴን እመራበታለሁኝ ቤተሰቤንም በተቻለን አቅም እረዳበታለሁኝ። ስለዚህ ለኔ ከሥራም በላይ ሕይወቴ ነው። ደስታዬም ነው። ይልቅ ያቺ ከወንደሰን ጋር የምትሔደው ሴት ስለውጪ ሀገር ምን ያህል ታውቃለች?

በለጠ፡- እ! ዮርዳኖስን ነው?... እስዋም የሱ ቢጤ ናት ውጪ የመውጣት ጉጉቷ እጅግ የናረ ነው። ከዛ ውጪ ምንም የምታውቀው ነገር ያለ አይመስለኝም።

እስክንድር፡- እሺ ይሁን ግን አብሮ በመውጣቱስ ምን ተባብለዋል?

በለጠ፡- ትቀልዳለህ ወንድሜ ምን ችግር አለ? እድሜ ለብር ብር እኮ ዛሬ ዛሬ እሳትና ጭድ ሳያገባ አይቀርም! ይገርምሀል የሁለቱ ፍላጎት ለየቅል ነው። ሳስበው ወንደሰን እስዋን እያፈቀራት ሳይሆን አይቀርም። እስዋ ደግሞ ግድ ካልሆነባት በቀር የምታስበውም አይመስለኝም>> /በነገሩ ለመሣቅ እየሞከረ/

እስክንድር፡- አንተ ይሔን በምን አወቅክ? /በመገረም ይጠይቀዋል/

በለጠ፡- እንዴት አላውቅም? በተገናኘን ቁጥር የሚያነሳብኝ እንደዚሁ ይመስልሃል?

እስክንድር፡- እና አንተ ምን ትለዋለህ?

በለጠ፡- ምን እለዋለሁ በቃ እሷም እየወደደችው እንደሆነ እነግረዋለሁዋ!

በመ/ገ/ጽ/ቅ/ጊ/ቤ/ክ/ስ/ት/ቤት
ኪነ ጥበብ ክፍል

እስክንድር፡- እንዴ ታዲያ አንተ ውሸት መናገር አግባብ ነው? /በመልሱ በመገረም/

በለጠ፡- ይሄ ምን ውሸት ነው ምንም ውሸት አይደለም! ይሔ ለመኖር ሲባ የሚፈጠር ተራ ቀልድ ነው።

እስክንድር፡- ታዲያ ምንድን ነው /ይበልጥ በመገረም ጭንቅላቱን እየነቀነቀ/ ጥሩ ያደረክ አይመስለኝም/ ይልና ሰዓቱን አይቶ ከተቀመጠበት ይነሳል/ በቃ ሰዓቱ በጣም እየሔደ ስለሆነ እኔ ልሔድ ነው ወንደሰንም ቀረ። /እንዳለ ከውጪ ድምጽ ይሰማሉ የሚናርው ገበየሁ ነው/

ገበየሁ፡- አጅሬው እየጠበቀህ ነው። የሚሸጥ ነገር ካለ ሳይፈልግ አይቀርም /እንዳለ ወንደሰን እየሳቀ ወደ ውስጥ ገብቶ/

ወንደሰን፡- እንደምን ዋላችሁ በሌ /ይልና በለጠን ትከሻ ለትከሻ እየተጋጩ ሰላም ይለዋል። እስክንድርንም እንደዛው ሰላም ይለውና/ እሺ በለጠ ጠፋህ ገበየሁ እኮ መምጣትህን እየነገረኝ ነበር መቼም ሁለታችሁም ትዋደዳላችሁ /ፈገግ ብሎ ይጠይቀዋል/

በለጠ፡- ምን ይሔ ጥጋበኛ አሁን እኮ እዚህ ሊደበድበኝ ምንም አልቀረውም ነበር /በንዴት/

ወንደሰን፡- በሱ ትናደዳለህ? ገበየሁ እኮ ገና ያልገባው ገጠሬ ነው መናገር እንጂ ምንም አያውቅ

በለጠ፡- እንዳስፈለገው አፉን እየዘረጠጠ ቀላል ሰው መስሎሃል።

ወንደሰን፡- ለዚህ ፋራ ገጠሬ እንዲህ ትሆናለህ ኧረ ይገርማል ገበየሁ እኮ አመለካከቱ ስልጣኔ ያልዳሰሰው አስተሳሰቡ ገና ትራዲሽናል ነውኮ! እርሳው ይልቅ ሰሞኑን ጠፋህብኝ ዮርዳኖስስ እንዴት ናት?

በለጠ፡- እርስዋማ ተወው መቼም ናፍቆቱ እየበረታባት ሳይሆን አይቀርም

ወንደሰን፡- እንዴት?

በለጠ፡- ትላንት አግኝቼአት ነበር እናም ወንደሰን ምነው ጠፋ አለችኝ።

ወንደሰን፡- ምን? አንዴ ከተገናኘን እኮ ገና 4 ቀን እንኳን አልሞላንም።

በለጠ፡- እኔስ ይህን አውቄ አይደል ናፍቆት በረታባት ያልኩት /በፈገግታ ይመለከታል/

ወንደሰን፡- ወይ አንተ! መቼም የገባህ እኮ ነህ/ በደስታ ተውጦ/ አለ እንጂ ያ ጓደኛዬ ሰማይን ከምድር ጋር እያጣመረ እሰው አእምሮ ላይ ፍርሃት የሚጥል። ገና ለገና ባህል፣ አገር፣ ታሪክ፣ ሃይማኖት፣ መናነት፣ የሚሉተረ ነገር እያነሳ ጆሮን የሚያደክም

በለጠ፡- ማነው እሱ?

ወንደሰን፡- መክብብ ነዋ!

በለጠ፡- እ! እሱን ነው እንዴ? ለመሆኑ አለ? ካየሁትም እኮ ቆየ!

በመ/ገ/ጽ/ቅ/ጊ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤት
ኪነ ጥበብ ክፍል

ወንደሰን፡- ባይገርምህ ብሶበታል ሁሌም ይጨቀጭቀኛል እንዴ እስክንድር ተጫወት እንጂ ምነው ዝም ብሎ ማዳመጡ ዘንድሮም አልተውክም? /ፈገግ እያለ ይጠይቀዋል/

እስክንድር፡- አይ እየሰማኋችሁ ስለሆነ ነው እንጂ እጫወታለሁኝ / ብሎ ይመልስለታል/

ወንደሰን፡- ለመሆኑ መክብብን ታውቀዋለህ?

እስክንድረ፡- ኧረ በደንብ ነው የማውቀው በጣም የምግባበውና የማደንቀው ሰው ነው።

ወንደሰን፡- ወይ ማድነቅ /ነገሩን እያጋነነ/ ወንድሜ አንተ አላወቅከውም ባትጋባባው ይሻልሃል።

እስክንድር፡- ለምን? /በመገረም ይጠይቀዋል/

ወንደሰን፡- ይገርምሀል አሰልቺ የሆነው የማንነት ጥያቄው እና ምክሩ ብትሰማው ሳያሳብድህ አይቀርም በተለይ ሃይማኖትህን በቅድሚያ እወቅ የሚለው መርህ ውይ! ውይ! አያምጣው! /በመሰላቸት ይናገራል/

እስክንድር፡- እንጃ የሚናገረው ንግግር ሁሉ ጠቃሚና እውነትነት ያለው መሆኑ ነው እኔ የሚገባኝ እናንተ እንደምትሉት ግን ይህን ያህል አሰልቺ ነገር አላየሁበትም።

ወንደሰን፡- ተወው እስክንድር እንኳንም አየኸው ይልቅ ሥራ እንዴት ነው? ብዙም አላይህም?

እስክንድር፡- ሥራ በጣም ደህና ነው ያው በሥራው ምክንያት ተጠፋፋን እንጂ እኔ እንኳን በጣም ነው ስለተሳካልህ በጣም ደስ ብሎኛል እንኳን ደስ አለህ። /ብሎ ተነስቶ ይጨብጠዋል/

ወንደሰን፡- /እየጨበው/ ኦ ቴንኪው! በጣም አመሰግናለሁ /ይላል/

እስክንድር፡- /ሰዓቱን እያየ/ ኦ! መቼ ነው የምትሔደው? ሰዓቱ በጣም ሔዷል በቃ እንሒድ

ወንደሰን፡- እንዴ! ምነው? ቆዩ እንጂ ማዘር ስትመጣ አብረን እንወጣለን።

በለጠ፡- አይደለም ወንዴ መሔድ አለብን እንደውም እስክንድር የምሔድበት አለ እያለኝ ስለነበር እንቸኩላለን ይልቅ ወንዴ ፊልጌህ ነበር የመጣሁት

ወንደሰን፡-	ምነው በሌ ምን ችግር አለ?

በለጠ፡-	አይ የሆነ ችግር ገጥሞኛል እናም ከዚያ ከሚቀረኝ ብር ላይ ትንሽ ብትሰጠኝ ፈልጌ ነበር መቼም ካለህ ላስቸግርህ ነው።

ወንደሰን፡-	ማስቸገር አትበል በለጠ ነገር ግን በኪሴ አልያዝኩም ቆይ እስኪ መኝታ ቤት ትንሽ ብር ሳይኖር አይቀርም ላምጣልህ /ብሎ ወደ ጓዳ ይገባል ከዚያም በለጠ ለእስክንድር እንዲህ ብሎ ይጠይቀዋል/

በለጠ፡-	ምነው ደበረህ እንዴ? /በአክብሮት እያስተዋለ/

በመ/ገ/ጽ/ቅ/ጊ/ቤ/ክ/ስ/ት/ቤት
ኪነ ጥበብ ክፍል

እስክንድር፡-	በጣም ደብሮኛል እጅግ አስጠልቶኛል /በመንገሽገሽ ይመልስለታል/

በለጠ፡-	ምኑ ነው ያስጠላህ?

እስክንድር፡-	በሆነው ባሆነው መዋሸቱ፤ በቀቢፀ ተስፋ ሰውን ማጓጓቱ፣ በገዛ ጓደኛ ላይ መሳለቁ፣

የሰውን ሥጋ መብላቱ፣ የሐሰት እራፊ መደረቱ፣ እንዴት ያስጠላል?

በለጠ፡-	ስለምንድን ነው የምታወራው? /እያፈጠጠ ይጠይቀዋል/

እስክንድር፡-	በለጠ ውሸት አይቀርም?

በለጠ፡-	የምን ውሸት?

እስክንድር፡-	ስለ መኩብብ፣ ስለ ዮርዳኖስ፣ ስለ ጉዞው ሁሉ የሚሰሙት ነገሮች ሁሉ አይቀፋም?

በለጠ፡-	ምንድን ነው የሚቀፈው የሚወራው ይወራል! የማይወራው የተዋል! ሌላ ነገር አለው? ለምን አይገባህም ዛሬን ለማደር አዳዲስ ነገሮችን መፍጠር፤ በቃ ከዚህ ሌላ ምርጫ የለም።.... ይልቅ አየህ አይደል? ስለ ዮርዳኖስ ሳነሳበት እንዴተር ደስ እንዳለው? /ፈገግ ለማለት እየሞከረ/ እንደውም ግድ የለህም ግምቴ ልክ ሳይሆን አይቀርም? /እስክንድር ግን ዝም ይለዋል አይመልስለትም በመገረም ብቻ ጭንቅላቱን ይነቀንቃል ወንደሰን ይመጣል ከዚያም/

ወንደሰን፡-	ይኸው በሌ ለጊዜው ያለኝ ይሔ ነው አባባ እስኪመጣ ብትጠብቅ ኖሮ እጨምርልህ ነበር

በለጠ፡-	/ብሩን ይቆጥርና/ በቃ ምንም አይደል ይሔ ይበቃኛል የቀረው ቀስ ብዬ እወስደዋለሁኝ /እንዳለው እስክንድረ ወደ በሩ እየሔደ/

እስክንድር፡-	ወንደሰን በቃ ደህና ዋል ቻው /ብሎ ሲወጣ ወንደሰን አፀፌታውን ይመልስለታል በለጠም ቻው ብሎት ሲወጣ/

ወንሰን፡-	በለጠ ስትወጣ ገበየሁን ጥራው! /ብሎ ያዘዋል በለጠም እሺ ብሎት የወጣል ከጥቂት ጊዜ /ደቂቃ/ በኋላ ገበየሁ ይመጣል/

ገበየሁ፡-	አቤት ፈለግኸኝ ወንዴ? ይላል አቋቋሙን እያስተካከለ/

ወንደሰን፡-	አዎ ፈልጌህ ነበር ስማ በለጠን ለምን ታስቸግረዋለህ? ለምንስ ትሰድበዋለህ?

ገበየሁ፡-	ችግር አለ! አ አስቸገረኝ ብሎ ተናረህ? /በመደነቅ ይጠይቀዋል/

ወንደሰን፡-	አላለኝም ግን እንደምትሰድበው ስለማውቅነው!

ገበየሁ፡-	ኧረግ እንዴ እኔ ምንም አልተሳደብኩም ለምንስ እሰድበዋለሁ? ...ግን እ!...

ወንደሰን፦ ግን ምን? ምን ዝም ያስብለሃል? ጨርሰዋ ....../ያፈጥበታል/



ገበየሁ፦ ማለቴ በቃ ጌቶች ቢፈቅዱልኝ በዚህ ዱላ አናቱን ብለው ደስ ይለኝ ነበር /ዱላውን አንስቶ እያሽከረከ እያየ/

ወንደሰን፦ ምን አልክ?...ኧረ መፈንዳት/ነገሩን ለማጋነን እየሞከረ/ አንተም ፈነዳህ? ቆይ ግን ምር አደረገኝ ብለህ ነው የምትመታው

ገበየሁ፦ ምንም አላረገኝም ግን ሳየው ቀልቤ አይወደውም!

ወንደሰን፦ ቀልቤ አልወደደውም! /እያሾፈበት/ አንተ ጠንቋይ ነህ ቀልብህ የማይወደው?

ገበየሁ፦ ኧረ እግዜር ይቅር ይበልህ እንዴ ምን ነካህ እኔ ባገሬ ጠንቋይ ለራሱ እንደማያእ አቃለሁ ነገር ግን ይሔ በለጠ ነገረ ሥረ ሁሉ የአታላይ ይመስላል

ወንደሰን፦ ታዲያ አንተ በምን አወቅክ?

ገበየሁ፦ እንዴ ወንደሰን እኔ እንደሱ ዓይነት ሰው ዝም ብሎ ቀልቤ አይወደውም በቃ ትኩር ብዬ ሳየው ችግር እንዳለበት ይሰማኛ! /ጭንቅላቱን በጥርጣሬ እየነቀነቀ/

ወንደሰን፦ በል ዝም በል ያንተ ችግር መቼም አያልቅም

ገበየሁ፦ እንደሱ ዓይነት ጓደኛስ ቢኧርብህ ይሻላል አትሰማውም እንጂ ያንተ ጓደኛ መክብብ ብቻ ነው ሌላው አታላይ ነው!

ወንደሰን፦ ኧረ ባክህ? /እያሾፈበት/

ገበየሁ፦ እውነት ነው የምልህ ታገሬ የወጣሁበት ቀን ይውቀሰን መክብብ ማለት የዝጌር ሰው ነው። /በጣም በማድነቅ/

ወንደሰን፦ በቃህ ይብቃህ ስለኔ አንተ አትነግረኝም ስማ ከአሁን በኋላ ስለ በለጠ አንድ ነገር ብትል ነግሬአለሁኝ ለፋዘር እንደምትሳደብ ነግሬው ጉድህ ይፈላል።

ገበየሁ፦ አረ እኔ ምን ደሎኝ እሺ በቃ ዝም እላለሁ አልናገርም / ብኮ አፋን ይይዛል/

ወንደሰን፦ አሁን ሒድልኝ እዚህ አትገተር

ገበየሁ፦ እሺ /ብሎ ለመውጣት ወደ በሩ ሲሔድ/

ወንደሰን፦ ስማ ቆይ ማዘር የት ሔዳ ነው?

ገበየሁ፦ ለዓመት በዓል የሚሆን ነገር ልሸማምት ብለው ነው የወጡት

ወንደሰን፦ ሲስተርስ?

ገበየሁ፦ ሲስተርም... አብራቸው ነው የሔደችው

ወንደሰን፡- አሁን ሒድ በቃ!

ገበየሁ፡- ኦኬ!... /ይልና በፍጥነት ወጥቶ ይሔዳል/

ወንደሰን፡- /መድረኩ ላይ ጥቂት ይቆያል ከጥቂት ደቂቃ በኋላ መክብብ ይመጣል በደንብሰላም ይባባላሉ ከዚያም/

ወንደሰን፡- ከትላንት ወዲያ ቸኩለህ ሔድክ በሰላም ነው ተጣድፈህ የሔድከው?

መክብብ፡- ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ስለነበረብኝ ነው የሔድኩት ይልቅ ጉዞው እየተመቻቸልህ ነው?

ወንደሰን፡- በጣም ተመቻችቶዋል ከአሁን በኋላ እኮ ፍላይ ማድረግ ብቻ ነው የቀረን ስልጣኔን ሀ ብዬ ልጀምር ጥቂት ቀን ብቻ /በደስታ ተውጦ ይናገራል/

መክብብ፡- ታዲያ ከሐገር ስልምትወጣ ሐዘንና ሃሳብ እንጂ ይህን ያህል ደስታ ም አመጣው?

ወንደሰን፡- ምን? አህ ሀ ሀ /ሳቅ/ ሀዘን? የምን ሀዘን ከሲኦል ስለምላቀቅ ሀዘን ይሰማኛል?

መክብብ፡- ሲኦል አልክ ወንደሰን.. ገና ለገና ባልተጨበጠና ባልተፈፀመ ነገር ትመካለህ? መመካት እኮ በእግዚአብሔር ነው። ከአገርህ ስለምወጣ ብቻ ይህን ያህል ጉራ ለምን አስፈለገ? እዚህም ሆነህ እኮ የምትበላው፣ የምትለብሰው፣ መጠለያ አላጣህም። ለምን ታማርራለህ? ካንተ የባሱት በየጎዳነው፣ በየቤተክርስቲያኑ በራፍ የወደቁት በየቤታቸው የታረዙት የተጠሙት የተራቡት ምን ይበሉ? ሕይወታቸውን በሰቀቀን የሚገፉት ምን ይበሉ? ተናገራ አንተ ምን አጣህ?

ወንደሰን፡- ምን አገኘሁ? ልሥራ ስትል ምቀኛው፣ ስታገኝ ምቀኛው ቅናተኛው መች ይቻላል። በራስህ አመለካከት እንዳትጓዝ ባህሉን አፈረሰ ሃይማኖቱን ጣሰ እያለ ስም ይሰጥሃል። ይሔ በረሱ የእድገት ማነቆ ነው። አቦ ተወኝ እንዲህ አይነት ኋላ ቀረ አመለካከት ባለበት ህብረተሰብ ውስጥ ምንኛ ይጨንቃል።

መክብብ፡- አየህ ወንዴ? ማንኛውም ህብረተሰብ ወስጥ የተሳሳተ አመለካከት የለም ማለት አይቻልም እናም ከአንድ ከምትኖርበት ህብረተሰብ ውስጥ ለብቻዬ አውቃለሁ! ከሌላው እሻላለሁ! እኔ ብቻ ትክክል ነኝ የምትል ከሆነ ተሳስተሃል። ይሔ የመጀመሪያ ስህተትህነው።

ወንደሰን፡- እኔ ነኝ የተሳሳትኩት? ቆይ ምን ለማለት ፈልገህ ነው?

መክብብ፡- አየህ የሌላው አመለካከት የአባቶች እምነታቸው፣ ባህላቸው ስህተት ነው ትላለህ እንዴ ሰው እኮ እንደራሱ እንጂ እንደጎረቤቱ አይኖርም!

ወንደሰን፡- ባክህ ተወኝ ድሮም አንተን አይገባህም አንተና መሰሎችሁ ስለማይገባችሁ ከዘመኑ ጋራ መራመድ አይሆንላችሁም ሁል ጊዜ ነፃነት፣ ሀገር፣ታሪክ፣ሃይማኖት ማለት ትወዳላችሁ

በመ/ገ/ጽ/ቅ/ጊ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤት
ኪነ ጥበብ ክፍል

እስኪ ተመልከተው አሜሪካ እንኳን ትላንት ተነስታ በመሥራቷ በዘመናዊ አመለካከት በመደበር ዛሬ አለምን ታንቀጠቅጣለች! ከዚህ የበለጠ ነገር እስኪ ምን አለ?

መክብብ፡- እኔ እኮ ግራ የሚገባኝ ለምን ነፃነት ተሰጠኝ ያለኝ ማንነቴ እኔነቴ ለምን አልተዘረፈም

ነፃነት አሰለቸኝ ነው የምትለው?

ወንደሰን፡- ነፃነት? ነፃነት እራሱ ምንድን ነው? ነፃነት ገንዘብ ይሆናል ታሪክ ሃይማኖት ማንነት ሕብረት ይሆናሉ? ወደድክም ተላህም ግን መጀመሪያ ብር ነው ወሳኙ ከነአባባሉም <<ዊዝ አውት መኒ ኖ ፈኒ ካለገንዘብ ደስታ የለም ለማለት

መክብብ፡- በፍፁም አትሳሳት ገንዘብ ብቻውን ደስታን አይሰጥም። ደስታ የሚገኘው በእምነት ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ሲቻል ብቻ ነው።  <<ገንዘብ መውደድ ግን የኃጢያት ሁሉ ነው አንዳንዶች ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ እራሳቸውን ወጉ ይላል ቅዱስ ጳውሎስ 1ኛጢሞ፥ ም፥6፥10 በደንብ ብንመለከተው ገንዘብን ሽተው ከሀገር ወጥተው በከንቱ የቀሩትም ሞልተዋል። እርግጥ ነው አገራችን እንደ አውሮፓውያን በዘረፈችው ሃብት ንብረት አልደመቀችም። ነገር ግን ለዐይን የማይታይ ሀብት አላት እርሱም እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ያለው ደግሞ ሁሉም አለው።  /ይላል በደስታ ስሜት/

ወንደሰን፡- ምንም የላትም ደሃ ናት! የገንዘብ ደሃ! የእውቀት የጥበብ ደሃ ናት! ድሮም ቢሆን የሌለን ነገር ስናወራ ነው ወደኋላ የቀረነው። ለነገሩ እንደ ሼባዎቹ መቀበጣጠር እንጂ አንተን መች ይገባሃል? /ይላል በብስጭት እየጮኸ/

መክብብ፡- እሺ እኔ እንኳን አይገባኝም  /ፈገግ እያለ/ ግን አንተ የሃገራችን ጥበቧን፣ ሥልጣኔዋን፣ ተፈጥሮአዊ ሀብቷን፣ መንፈሳዊ እሴቶቿን፣ ቤተ ክርስቲያኗን ገዳማቷን መች ጎበኘህ? ምኗን አወቅክ? ሃይማኖትህንስ መች አወቅካት ይልቅ ያለህን ሀብት ሳታጣጥም የሰውን ስታደንቅ ዘመኑ እንዳያልፍብህ?

ወንደሰን፡- /በግርምት እያፈጠጠበት/ ሃይማኖት ገዳማት በቃ ከነዚህ በቀር ከአፍህ አይወጣም ማለትነው? ድሮም መሰሎችህ ይህን ዓይነት አስተሳሰብ እያሰቡ ነው በድህነት የሚፈጁን ይልቅ መክብብ ቢገባህስ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰው ሆኖ ከመፈጠር አሜሪካን ሀገር ዛፍ ሆኖ መብቀል ይሻላል።

መክብብ፡- ለነገሩ አይፈረድብህም ሰው እድገቱና ኑሮውን ይመስላል። ግን ብታምንም ባታምንም ዝቅ ዝቅ ያለ ከፍ ከፍ ይላል ። ከፍ ከፍ ያለ ዝቅ ዝቅ ይላል።

ወንደሰን፡- ይሔ ደግሞ ምን ማለት ነው?

መክብብ፡- ግልጽ ነው! ዓለም የናቃት የገዛ ልጅዎችዋም የዘነጓት ሀገር እርስዋ የማእዘን ድንጋይ ናት። ከሞት ይልቅ ሕይወት ይሰበክባታል።  ዛሬ ድሃ ብትሆንም አንድ ቀን እስዋም ያልፍላታል። ግን የሚገርመኝ ነገር ቢኖር ዛሬ ዓለም ስለኛ ለማወቅ ወደኛ ይጎርፋል

በመ/ገ/ጽ/ቅ/ጊ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤት
ኪነ ጥበብ ክፍል

በታሪካችን በሃይማኖታችን ሲደነቅ እኛ ደግሞ በዓለም እንደነቃለን። የኛን ጥላን የነሱን እናንጠለጥላለን። ብናውቅስ የምንከበረው የራሳችንን በመናቅ አልነበረም መቼም ቢሆን ማንነትን እረስቶ ስልጣኔ ከየት ሊመጣ?

ወንደሰን፡- እኔ እኮ ቅድም ነግሬህለሁኝ መክብብ አንተ ግን አይገባህም /በገድ የለሽነት/

መክብብ፡- ምኑን ነው የነገርከኝ?

ወንደሰን፡- አየህ እንደሼባ መነዛነዝ ብቻ ነው የምታውቀው ይልቅ በወጣትነትህ ንቃበትለለ በኢትዮጵያዊነትህ ውርደት፣ አንገት መድፋት ብቻ ነው የምታገኘው።

መክብብ፡- ስማ እናትህ ስላጣች፣ ስለደኸየች፣ ስላረጀች፣ ስለተጎሳቆለች እናቴ አይደለችም ትላታለህ? እንዲህ ብትላት የጠባሃቸው ጡቶቿ ይፋረዱሃል፤ ይህን መቼም ቢሆን አትክትድ! /ብሎ እንደጠየቀው በሩ ተንኳኩቶ ወደ መድረኩ አንዲት ሴት ትመጣለች ሴቷ የወንደሰን አብሮ አደግ ናት ስምረት ትባላለች ስምረት ስትገባ ሃይ ሃይ እንደምን ዋላችሁ ብላ ሁለቱንም በመሳም ሰላምታ ይለዋወጣሉ ከዚያም/

ስምረት፡- ምነው ምን እያወራችሁ ነበር አቋረጥኳችሁ አንዴ?

ወንደሰን፡- ምን እባክሽ ይሔ በሙግት የሰውን አእምሮ በከንቱ ይበጠብጣል /ይላል እያጣጣለው/

መክብብ፡- ወንደሰን ይሔ ሙግት አትበለው የምናገረው እውነት ነው። ወደድክም ጠላህም ሀገርህ እናትህ ናት። አንተ ከኔ ከሐገር ስለምትወጣ ብቻ ሀገርህ መናቅ ያለባት አይመስለኝመ የገዛ አንተነትህን ብትክድ ብትክድ ጉዳቱ ለራስህ ነው። እኔ እያልኩህ ያለሁት እራስህን እወቅ ነው። የምዕራባውያን ስልጣኔ ሥጋወ ነው። የኛ ግን ማንነት ሙሉ መንፈሳዊነት ነው። ይህን እንዳትክድ ነው ያልኩህ፤

ወንደሰን፡- በናትህ ተወኝ /በብስጭት/ በትላት ዛሬ አይኖርም ትላንት አልፏል። ይልቅ ዛሬን እንደሰትባት ዛሬን ለመደሰት ደግሞ ደስታ ወዳለበት መጓዝ ነው። እዚህ ሀገር ዞር ስትል የምታየው ርሃብ፣ ብሶት፣ ለቅሶ፣ ሰቆቃ፣ ብቻ ነው። So /ስለዚህ/ ወደ ደስተኞቹ መፈርጠጥ! አይደል እንዴ ስምረት? /ለስምረት ይጠይቃል/

ስምረት፡- ልክ ነህ ወንደሰን እንዴ እዚህ ሀገረር ለመሥራት ስንትና ስንት ችግር አለ በናትህ?

መክብብ፡- አንቺ ደግሞ ምን ሆንኩ ልትይ ነው? /በግርምት ይጠይቃታል/

ስምረት፡- ምን የማልሆነው አለ? ይገርምሃል ባለፈው እንኳን የገጠመኝን ብነግርህ እ! የሆነ ቦታ ሥራ ለመወዳደር ሔጄ ነበርለለ ታዲያ የጥያቄያቸው ብዛት በራሱ አንድ የፊክሽን መጽሐፍ ይወጣዋል። እስኪ በናትህ ኮሌጅ ገብቼ የተማርኩት ለአንድ ሥራ አይደለም? እስኪ ምን አለበት ዝም ብለው ቢያስገቡኝ? እሺ ይሁን ብዬ ጥያቄውን እንደምንም አለፍኩና ገባሁ ታዲያ የምትሰራው ሥራና የምታገኘው ገንዘብ መች ሊመጣጠን ብቻ ተወው ስንት ችግር አለ መሰለህ። ከዚህ ሁሉ የተሻለ ነገር መፈለግ ሳይሻል ይቀራል? በማለት እኔም ልቀየስ ነው።

በመ/ገ/ጸ/ቅ/ጊ/ቤ/ክ/ስ/ት/ቤት
ኪነ ጥበብ ክፍል

መክብብ፡- ታዲያ ኮሌጅ ተመርቆ መውጣት ብቻውን በቂ ነው ትያለሽ?

ስምረት፡- ኦፍ ኮርስ! እንዴት በቂ አይደለም? ዓመታት የተማርኩት እኮ አንድ ሥራ ላይ ለመቀመጥ ነው! /ትላለች በእርግጠኝነት መንፈስ/

መክብብ፡- ልክ ነሽ ስምረት የተማርሽው ለመሥራት ለመለወጥም ነው። ነገር ግን ስንቱ ነው በትክክል የተማረው ስንቱ ነው እውነተኛ የሆነ የመማር የመለወጥ እራሱንና ቤተሰቡን እንዲሁም አገሩን ለመርዳት ያሰበው። እነኔ እንደምመለከተው ግን ከሚማሩት ግማሾቹ በየመዝናኛው ቦታዎች በየካፍቴሪያው ጊዜያቸውን በከንቱ ሲገሉ ነው የሚታዩት ስለዚህ እነዚህ በሙሉ ተማሪዎች እውነተና ዓላማ ያላቸው ናቸው ማለት ይከብደኛል። ስለዚህ በሥራ ለመቀጠር ፈተናው ተገቢ ነው ደግሞስ በአንዴ መክበር በቀላሉ የሚታሰብ ነገር ይመስልሻል።

ስምረት፡- የስ ማንም ቢሆን እስከሰራ ድረስ በባቂ ሁኔታ የድካሙን ማግኘትና ውጤታማ መሆን አለበት።

መክብብ፡- እኔ እንኳን አይመስለንመ ሰው መክበር ያለበት በገንዘብ ሳይሆን በሥራው ነው። ቀስ በቀስ ደግሞ በሥራ ውጤት ይገኛል። ተስፋ ማድረግና እግዚአብሔርን መለመን ነው ተገቢው ክርስቲያን ኑሮው በመጠን ነው። በመጠን ስንኖር ትንሹ ነገራችን በበረከት ይሞላል።

ወንደሰን፡- /በመሰላቸት ዓይነት/ ይኸውልሽ መሸበክ ጀመረው ይሔ ሰው እኮ ቀስ በቀስ ቄስ ሊሆን ነው ዋይ!ዋይ! ይቺ ሀገር የማታበቅለው ፈላስፋ የለም በቃ?

መክብብ፡- ፈላስፋ አትበል ይሔ ፍልስፍና አይደለም! /ንግግሩን ጠበቅ እያረገ/ የተናገርኩት የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን ነው። የእግዚአብሔር ቃል የማንነታችን መገለጫ ነው። ብዙ አባቶቻችንና እንቶቻችን ያለ እግዚአብሔር አልተገዙም። ዛሬ ግን የኛ ትውልድ ተቃራኒዎች ሆነናል። የሌሎችን እያመለክን የራሳችንን እየጣልን መሆኑን አሁንም ተረዳው።

ወንደሰን፡- እንግዲያውስ የፈለከውን ብትቀባጥር ግድ አይሰጠንም እና ከሀገር መውጣታችን አይቀርም። ምን አልባት ከውጪ አንድ ቀን ስንመለስ እዚሁ በተቀመጥክበት ስፍራ ይሔንን ልብስ እንደለበስክ እዚሁ ቦታ ላይ ሳናገኝህ አንቀርም /ፈገግ እያለ/

ስምረት፡- /እርስዋም ፈገግ እያለች/ እኔም የሳውዲ አረቢያው /የጂዳ/ ጉዞዬ እየተጠናቀቀ ነው፤ ሦስት ዓመት ሰርቼ ስመጣ እንደማስበው አማካሪ ሳያስፈልገኝ አይቀርምና አደራህን ያኔ እንዳላጣህ! /ሁለቱም ይስቃሉ/

መክብብ፡- ሃሳባችሁ በጣም ጥሩ /እሱም ፈገግ እያለ/ ግን ይሆናን ስታስቡ አይሆን ይሆን ብላችሁ ማሰቡን አትርሱ። ደግሞም ልነግራችሁ የሚፈልገው ነገር ቢኖር የእግዚአብሔርን ጥበብ ማንም አይመረምርም እኔም ጠንክሬ ብሰራ ሕይወቴን አሻሽል ይሆናል! ባይሆንም የሱ ፈቃድ ነው ብቻ ደህና ይግጠመን በሉ

በመ/ገ/ጽ/ቅ/ጊ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤት<br>ኪነ ጥበብ ክፍል

ወንደሰን፡- ደግሞ ምን ሊገጥመን ? /በንቀት/

መክብብ፡- የሰው ሀገር የሰው ነው። በሀገራችሁ ያለው ነፃነት የሰው ሀገር አይደገምም። እንዲሁም ከምንም በላይ አገራችሁንና ወገኖቻችሁን ልታስቡ ያስፈልጋል። እናታችሁ ምንም ቢሆን ከእንጀራ እናት ትበልጣለች ብሎ ሰዓቱን ይመለከታል ከዚያም አሁን የሆነ ቦታ ደርሼ ልምጠያ የቀጠሮ ሰዓት ደርሶብኛል። እመለሳለሁ እስከዛው ግን ቻው!! ብሎአቸው እየተቻኮለ ይወጣል። ለማንኛውም ከሀገር በመውጣታችሁ ባላችሁበት ቦታ የክርስቶስን ልደት በቤ/ክ እንድታከብሩ አብዝታችሁ ቃሉን ተምራችሁ ሀሰትን ተላብሳችሁ

ወንደሰን፡- /ሲወጣ እያስተዋለው ይቆይና/ ወይ መክብብ ጊዜውን በከንቱ የሚጨርስ ሰው ሆነ በቃ ይጮግራል እንዴ የገና ዕለት በዛን ዕለት

ስምረት፡- እንዴት ወንደሰን? /ተክዛ ትጠይቀዋለች/

ወንደሰን፡- አትሰሚውም? እስኪ በዚህ በ 21 ኛው ክፍለ ዘመን ሃይማኖት ታሪክ ባህል የሚባሉት ነገሮች ምን ዋ አላቸው። ዘመኑ እኮ የግሎባላይዜሽን ነው፤ ዓለም አንድ መንደር ናት ይታይሽ ዋናው ነገር ሰርቶ መለወጥና በቀላሉ ብር ማፈስ ነው። ያለ ብር ይህ ዓለም ምን ቦታ አለው?

ስምረት፡- እርግጥ ልክ ነህ! ግን አንዳንዴ የመክብብም ንግግሮች ከልብ ከተሰሙ እውነት ናቸው።

ወንደሰን፡- ኧረ እንዴ ስምረት ፈራሽ? ምን ሆንሽ? መክብብ የቀባጠረው ሁሉ እውነት ይመስልሻል።

ስምረት፡- መፍራቴ እኮ አይደለም

ወንደሰን፡- ታዲያ ምንድን ነው የምትይው? እሱ ስለተናገረ ነው እንዲህ የምትሆኝው? አስቢ እንጂ ስምረት እዚህ ሀገር ጊዜሽን ከማቃጠል፣ በችግር ከመቆራመድ የተለየ አየር መተንፈስ በራሱ እኮ ትርጉም አለው። ስምረትን! /ለማግባባት እየሞከረ ይናገራታል።

ስምረት፡- እሱማ ልክ ነህ እዚህ ሀገር ላይ እያከኩ ለመኖር የሰው ሀገር ባሪያ ሆኖ መኖር ይመረጣል።

ወንደሰን፡- አዎ ስምረት ታውቂያለሽ አብሮ አደግ ጓደኛችን ዳንኤል እንኳን አቋራርጦ ደቡብ አፍሪካ ገብቶ በደስታ እንደሚኖር ባፈልኝ። እኔ ግን እዚህ ወይኔ ወንደሰን!! ብቻ ተያው አንድ ወር ነው የቀረኝ እኔም እወጣለሁ።

ስምረት፡- ወንደሰን ግን እኮ የሰው ወሬ ማዳመጥ ምንም ዋጋ የለውም። ነገሮችን መክብብ እንዳለው በጥንቃቄ መመርመር ነው። ለሌላው ስለተሳከ ለኔም ይሳካል ማለት ይከብዳል።

ወንደሰን፡- ተይው ባክሽ! እሱ ሁሌም ሰውን እንዳስፈራራ እሱም እንደፈራ ነው። ስንቱ ነው ከሐገሩ ወጥቶ የሚኖረው?

ስምረት፡- ቢሆንም መጠንቀቅ ተገቢ ነው። አስብበት በል አሁን ልሒድ የመጣሁት እህትህን ፈልጌያት ነበር የለችም አይደል? /ብላ ትጠብቀዋለች/



ወንደሰን፡- የለችም ከማዘር ጋር ነው የሔዱት እኔም እነሱን እየጠበኩ ነው።

ስምረት፡-በቃ ልሒድ ሲመጡ እደውላለሁ ቻዎ! /እየወጣች ቻው ትለዋለች/

ወንደሰን፡- /ቻው! ይላታል። ከዚያም ወንደሰን ጠረጴዛ ነገር ላይ መጽሔቶችን ነካ ነካ ያደርግና ይተዋቸዋል ከሚያም/ ማዘር ደግሞ አትመጣም እንዴ ይህን ያህል ጠብቄያት ይልና ሰዓቱን አይቶ ወንበሩ ላይ ተመቻችቶ ሲቀመጥ በደቂቃ ውስጥ እንቅልፍ ሸለብ ያደርገዋል። በዚህን ጊዜ ከመድረኩ በስተጀርባ አንድ ድምጽ ይጮኻል /እንዲህ እያለ/

ድምፅ፡- አንተ የተኛህ አትሰማም?! አንተ ያንቀላፋግ አትነቃም?! እማን ላይ ተቀምጠህ ማንንስ ታማለህ? /ይላል ያ ድምጽ በጩኸት/

ወንደሰን፡- /በድንጋጤ መንፈስ ከተቀመጠበት ተስፈንጥሮ ይነሳና ያማትባል/

ድምጹ፡- /እንደገና/ ታማትባለህ አህ አህ ህ /ሣቅ/ ማማተቡ ከየት ለመድረስ፣ ማን ነው ያስተማረክ? ቆመህ ሳለ ያንቃለፋህ፣ አንተ በቀመናህ የሞትክ፣ የእሳት ልጅ አመድ! /ይላል ያ ድምጽ በጩኸት/

ወንደሰን፡- /ንግግሩን እያቆራረጠ በፍርሃት ስሜት ተውጦ/ ማ... ማ... ማነህ ማነሽ አንቺ

ድምጹ ፡- ማንነቴ ምን ሊጠቅምህ? ብነግርህስ ምን ሊረባህ? እንኳን ስለ እኔ ስለራስህ ምን ታውቃለህ?

ወንደሰን፡- /ግራ በመጋባት የሚሆነውን ያል እየተሿሿረ አካባቢወን ይቃኛል/

ድምጽ፡- ተናገራ ወኔህ ሁሉ ምን ሰለበው? ያ እውቀትህስ? ያ ጉራህስ የት ከተትከው? እንዳላዋቂ ስትንቀኝ፤ አንደሞኝም ስትስቅብኝ፤ በታሪኬ መቀለድህ፣ ባህሌንም ማዋረድግ በኔነቴ መሳለቅህ ለመሆኑ አንተ ማነህ? እኔን የናቅክ በኔነቴ የተሳለክ? ተናገራ! ብታውቅስ ማንነትህ ያሳደግሁህ እኔው ነበርኩ ብትራብም ያበላሁህ ብትጠማ ያጠጣሁህ ብትታረዝ ያለበስኩህ በልጅነት የጠበቅሁህ እስከዛሬው ያደረስከህ ኤነው ነበርኩ ብትረዳው ሥጋ አጥንትን ሙሉ አካልህ ታዲያ ማነህ እኔን የናቅክ በኔነቴ የተሳለክ? ተናገራ! ምነው ዝም አልክ?! /ይላል በጩኸት/

ወንደሰን፡- /ግራ በመጋባት/ ም....ምን ልና..ገር□ ምኑን ላ..ውራ /ይል ንግግሮቹን እያቆራረጠ/

ድምጹ፡- ለመሆኑ አንተ ማነህ? የቱ ነው ሃይማኖትህ? ለምንስ ነው መፈጠርህ? ምናዊስ ነው ዜግነትህ?

ወንደሰን፡- ኦ...ኦርቶዶክስ ደግሞ እ...እ...ኢትዮጵያዊ ነኛ

ድምጽ፡- ኦርቶዶክስ ኢትዬጵያዊ አሃ ሃ ሃ... /በመገረም ይስቅበታል/ ኢትዮጵያዊ አልክ አንተ ከንቱ እነተማ እንደ አንተ አይነቱን መች ወለድኩኝ? አኔማ በማንነቱ የሚከሮ፣ የአምላኩን ስም የሚጠራ የሀገር ፍቅ የሚገባው፤ ዳር ድንበሩን የሚያስከብር፣ በሃይማኖቱ የማያፍር የሚለፋ ሰርቶ የሚያድ የሰውን ገንዘብ የማይመኝ ነበር የወለድኩት፡፤ ገና ዛሬ እንደ አንተ

ዓይነት ተፈጠረ። ለዓለም ስብከት የሚያድር፤ እንደራሱ የማያድር የበላበትን የሚሰብር ሰዓታቱን እየሻረ ሃይማኖቱን የሚቀይር፤ ህገ እግዚአብሔርን የሚያቃልል፤ በዝሙት ጠንቅ ሕፃናትን የሚገድል መጠን አልፎ የሚሰክር ጫት ሲጋራን የሚያባርር በዚህ ዘመን ፈጠርኩና አንገት ደፋሁ ላልቃና /ትላለች ኢትዮጵያ/

ወንደሰን፡- ኧረ ባክሽ ተይኝ /በመለማመጥ/ ምን አርገ ነው የምትይኝ ደግሞስ አንቺ ማነሽ? ምን ፈለግሽ? /ይላል በንዴት በመበሳጨት አይነት/

ኢትዮጵያ፡- እኔማ በድህነቴ የሳቅኩብኝ፤ አንደሞኝም የቆጠርከኝ፤ በባህሌ፤ በታሪኬ፤ በሰርዓቴ፤ በሃይማኖቴ፤ የሰደብከኝ ያዋረድከኝ። ብትተወኝ የማልተውህ፣ ብትገፋኝ የማልገልህ፣ ብትረግጠኝም የማልረግጥህ፣ እንደ ጥላህ የምከታተልህ እናትህ ነኝ። አዎ እናት ሀገርህ ኢትዮጵያ ነኝ።

ወንደሰን፡- ኢትዮጵያ!.....? / ይላል በመደነቅ እና ግራ በመጋባት

ኢትዮጵያ፡- አዎ ኢትዮጵያ! ይሔ ትውልድ የዘነጋኝ፣ መሰሎችህ የካዳችሁኝ ኢትዮጵያ ነኝ! ይሔ ዓለም ሲፈጠር ቀን ሲቆጠር ያኔ በአምላክ ፈቃድ ዓለም ሲበጅ በሕይወት ወንዝ አጠገብ ነበርኩ በጊዮን ወንዝ እንደተከበብኩ ተፈጥሮዬም ምድራዊ ብቻ ሳይሆን ሰማያዊ ነበር። ያኔ በሙሴ መጽሐፍ የተጻፈ የተጸፍኩ፣ የከ፣የያፌት፣ የሴም ዘር መገኛ የኖህ የቃል ኪዳን መታወሻ የአረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ መለያ እነሙሴ፣ እነኤርሚያስ፣ ቅዱስ ዳዊ፣ የሚያነሱን የናት ማክዳ፣ የሳባ ሀገር፣ በህገ ልቦና፣ በኦሪት ህግ፣ በሐዲስ ኪዳን በተዋህዶ ፀንቼ ያለሁ ኢትዮጵያ ነኝ። ከ 7 ሺ ዓመት በፊት የነበርኩ ዛሬም ያለሁ እግዚአብሔርን የማመልክ እስከ ዛሬ የነበርኩት የኢትዮጵያዊያን እናቶች ነኝ።

ወንደሰን፡- እና! እና! ምን ሆንሽ? ምን አርገ ነው የምትይኝ?

ኢትዮጵያ፡- እኔማ ዛሬ ልትሰሙኝ እወዳለሁ ልታዳምጡኝ እጓጓለሁ አንተ ትውልድ ማንነትህን ጠይቅ ሃይማኖትህን እወቅ፣ ሀገርህን አትናቅ፣ ሰላምና እረፍትህ በቅዱስ ኪዳን እንጂ በዘፈንና በጨዋታ በዋዛና በፈዛዛ አገርህና ነፃነትህን በዓለማዊ ተድላ ደስታ በሥጋዊ እውቀትና ጥበብ አይገኝም። ይልቁንም እምነትህን፣ ባህልህን፣ ሪክህን፣ ማንነትህን፣ በምትጓዝበት ሁሉ በምታርፍበት ቦታ ሁሉ ልታስበው ግድ አለብህ! አንድ ሰውም መነሻውን ካላወቀ መድረሻውን አያውቀውም ማንኛውም ሥራ የሚሰራው የቀደሙትን ዎች መሠረት በማድረግ እንጂ የሰው በማወደስ የራስን በማንኳሰስ መች ይሆናል? አንድ ሀገር ማንነቷን ካላወቀች የትም ልትደርስ አትችልም። አንተ ትውልድ ንቃ ማንነትህን ስታውቅ የፈጠረህ አምላክ ያኔ እርሱ መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊውን ጥበብ ይሰጥሀል፡፤

ወንደሰን፡- እኮ እኮ! እንዴት እንዴት! ብዬ ማንነቴን ልወቅ፣ ማንነቴን እንዴት ብዬ ልረዳው?

ኢትዮጵያ፡- ሐድ ልወቅ ካልክ ምን አጣህ? ልቅ ካልክ ማን ከልክሎህ? ቤተክርስቲያን ሐድ መጽሐፍቷን አንብበህ ስልጣነተዋን፣ እምንቷን፣ ስርዓቷን አንተነነትክን እንድትረዳው በረዥሙ ህልውናህ

በመ/ገ/ጽ/ቅ/ጊ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤት
ኪነ ጥበብ ክፍል

የሚታደግህ

ከመጥፋትም የታደገህ

በድል ላይ ድል ያጎናፀፈህ

አሁንም ለድል የሚያበቃህ

የኢትዮጵያዊነትህም ሃይማኖትህ ነው። እምነትህም ተዋህዶ ጠባቂህም ክርስቶስ ነው። አማለጅህም ድንግሊቱ ማሪያም ናት፤ ሀገርህም እናትህም ማንነትህ ሉለመናህ ኢትዮጵያ ሀገርህ ናት። /ድምጹ እየሰለለ ይሔዳል/ ከዚያም ፀጥ ይላል ድምፁ/አሁን እናም ለበአሉ ልትሄድበት ካሰብከው ቦታ ቀርተህ የክርስቶስን ልደት በቤቱ አክብር ቃሉን ስማ ዘምነር አመስግን ስለ ክርስስ መወለድ ትምህርት አንዲ ትጨፍር፣ትዘፍን ዘንድ አይገባም ገባህ!

ወንደሰን፡- አዎ አዎ

ኢትዮጵያ፡- በረዥሙ ህልውናህ

ከመከራ የወጣህ

ከመጥጋትም የታደገህ

በድል ላይ ድል ያጎናጸፈህ

የኢትዮጵያዊነት አርማህ ብቻ ነውና

በእምነትህና በእውነት ላይ ፅና

ኢትዮጵያዊነትህም ሐይማኖትህ ነው፤ እምነትህም ተዋህዶ ጠባቂህም ክርስቶስ ነው፤ አማላጅህም ድንግሊቱ ማርያም ናት፣ ፤

ሀገርህም እናትህም ማንነትህም ሁለመናህ ኢትዮጵያ አገርህ ነኝ (ድምፁ እየሰለለ እየቀነሰ ይሔዳል።) ከዚያም ፀጥ ይላል ድምፁ።

(ወንደሰንም ይንበረከክና ይወድቃል፤ ከዚያም ከተንበተከከበት ቀና እያለ እንዲህ ይላል)

ወንደሰን፡- <<ወይ ከንቱንት ለካስ በከንቱ ነው መመካቴ (እየተነሣ)

ሉብርና ለጌጣጌጥ መጓጓቴ

ማንነቴን ሳልረዳው

እኔነቴን ሳልጨብጠው።

ነበር ላካ ከንቱ ምኞት

ጉራ ብቻ የሞት ሕይወት፣፤ (ትንሽ አሰብ ያደርግና)

በመ/ገ/ጽ/ቅ/ጊ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤት

ኪነ ጥበብ ክፍል

ስንቱ ይሆን እንደኔ ያለው

በሚያየው ሉቡ ጓጉቶ የምንዝር ጌጥ ያጠለቀው

ስንት እንሆን በላማወቅ የጠፋነው

ጠቢብ መስለን ሞኝ የሆነው 2 }

(ብሎ ንግግሩን ይቋጫል። በመሃሉ መክብብ ይመጣል መክብብ የወንደሰንን አኳኋኑን ተመልክቶ)

መክብብ፡- ምነው ወንደሰን ምን ሆነሃል? (ይለዋል በማጋባት ስሜት)

ወንደሰን፡- << ምንም አልሆንኩም መክብብ አየህ መክብብ ያልከኝ ሁሉ እውነት ነው። አየህ ባለማወቅ የተጎዳሁት እኔ ነበርኩ ሌላው አያውቅም እያልኩ ሳላወቅ የጠፋሁት እኔው ነበርኩ። አሁን ግን ማወቅ እፈልጋለሁ ጊዜው ሳያልፍብኝ፣ ቀኑም ሳይጨልምብኝ ና እንሒድ> (ይላል ፊቱ ላይ አዲስ የለውጥ መንፈስ እየታየበት)

መክብብ፡- (በሁኔታው ግራ በመጋባት) <<እንዴ ወንደሰን የት የት ነው የምንሔደው?>>

ወንደሰን፡- <<ወደ ቤተ ክርስቲያን ሆነ ወደ ጥበብ አውድሞች ሁሉ ነዋ ! >>

መክብብ፡- <<ምን አልክ ? እየቀለድክ ነው? >> (ይለዋል በመደነቅ)

ወንደሰን፡- እየቀለድኩ አይደለም መክብብ የትም ከመሔዴ በፊት ስለ አገር ማወቅና ማንነቴን መረዳት አለብኝ።>>

መክብብ፡- (በደስታ መንፈስ ተውጦ) <<ተመስገን! አምላኬ ተመስገን! የሚሳንህ ነገር የለምና ውዳሴ ለአንተ ይገባል>> (ከዚያም ዞር ብሎ ለወንደሰን) <<እንግዲያውስ በል ና! እንሒድ ፈቃደኛ ከሆንክ ቤታችን ሁሉንም በፍቅር ትቀበላለችና! እንሒድ!>>

ወንደሰን፡- <<እሺ እንፍጠን ሳይመሽ እንገስግስ! እንሒድ!>>

(ተባብለው ሁለቱም እየተቻኮሉ ከመድረኩ ወጥተው ይሔዳሉ)

ድራማው በዚህ ያበቃል

አነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስጨረሰን ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው። አሜን!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ተሾመ ፍሰሐ

ግንቦት 7/1996 ዓ.ም

___________//__________

<u>የፁሑፎ መነሻ ሃሣብ፡-</u>

- ኢትዮጵያዊ በማንነቱ ፍለጋ>> የሚለው መጽሐፍ ነው።

<u>መፅሐፉ፡-</u>

- በንቡረዕድ ኤርሚያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ የተዘጋጀ መፅሐፍ ነው።